*ሰሞነኛ*

# ቅጡ የጠፋበት የኢትዮጵያ የዲያስፖራ ተቃውሞ

ዴሞክራሲያዊ፣ ምክኒያታዊና በዕውነት ላይ የተመረኮዘ ተቃውሞ የሀሳብ ፍጭትን በመጋበዝ የነጠሩ የተሻሉና አገርን የሚጠቅሙ ጭብጦችን በመፍጠር የሁሉም ነገር ግብ የሆኑትን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገትን እንደሚያመጣ ይታመናል:: ይህም በመሆኑ አያሌ ለዲሞክራሲ የቆሙ ወገኖችም ሆኑ አገሮች፣ የተቃዋሚ አካላትን መኖር እንደ አንድ ጠንካራ የዲሞክራሲ ስርዓት መገለጫ ይወስዱታል:: ከመውሰድም አልፈው በተለያዩ አገሮች የተቃዋሚ አካላትን እንዲኖሩ የሚያደርግ ስርዓት እንዲዘረጋ አጥብቀው ይሰራሉ::

እነዚህ በልማታቸው የገፉ አገሮች በረዥም ጊዜ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጉዞአቸው ያዳበሩት ልምድ፣ አስተማማኝ የዲሞክራሲ መዋቅርም ሆነ ስርዓት እንዲፈጥሩ አስችሏቸዋል:: ፓርቲዎች በሚያቀረቡት ፕሮግራምና በምርጫ ወቅት በሚያሳትፉት ሰዎች አማካኝነት በስልጣን ላይ መውረድና መውጣት አዲስ ነገር ሳይሆን የተለመደ ፖለቲካዊ ተግባር ነው:: ይህም የዳበረ የዲሞክራሲአዊ መግለጫዎች ከሚባሉት ተግባራት አንዱ ነው::

በእነዚህ አገሮች ፖለቲካዊ ክርክር ሆነ ተቃውሞ ለአገር ይበጃል ብለው በሚያስቧቸው አካሄዶች ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ሁሉም ክርክር ሆነ ተቃውሞ በህገ-መንግስቱና በተቀመጡ ህጎች ይዳኛል:: በዚህ አልመራም ያለ ወደ ክርክርም ሆነ ወደ ምርጫ ሲመጣ አይታይም:: ቢመጣም በህዝብ ዘንድ አመኔታና ተቀባይነት ስለሌለው ተፅዕኖ ለማሳደር አቅም የለውም::

ይህ ከላይ ለመነሻ ያህል የተቀመጠው ያደጉ አገሮች ዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የረዥም ጊዜ ውጣ ውረድና ትግል ውጤት መሆኑ ልብ ላለ በታዳጊ አገሮች ላይ እንከን አልባ ሆኖ በተግባር ላይ ለመተርጎም አያሌ ችግሮች ይፈታተኑታል:: «ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም» እንደሚባለው፣ ታዳጊ ዲሞክራሲያዊ አገሮች ዙሪያ መልስ የልማት፣ የሰላም ጥረታቸውና ግብግብአቸው እዚያው እንዳለ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነቡ የግድ ይላቸዋል::



**Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia**
**3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010**
**Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org**
**www.ethioconsulate-la.org**

## ሰሞነኛ

አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 16 ዓመታት የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን እንደዋነኛው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ አድርጋ የወሰደችው ለፋሽን ወይም ሌሎች አገሮችና አካላትን ለማስደሰት ሳይሆን፣ በአገራችን ለውጥ ለማምጣት የተጀመሩ የልማትና መልካም አስተዳደር ትግሎች ዲሞክራሲ ለውጥን ስለሚሹ ነው:: ስለዚህ በአገራችን ልማትና ሰላም የህልውና ጥያቄ እንደሆኑት ሁሉ፣ የዳበረ ዲሞክራሲአዊ ስርዓት መገንባትም በዚያው እኩል የህልውና ጥያቄ ነው:: ስለዚህ ዲሞክራሲ ለኛ ምንም ይሁን ምን ከልማታችንና ከሰላም ትግላችን ነጥለን አይተነው አናውቅም::

ከእነዚህ ምክኒያታዊና ዲሞክራሲአዊ መርሆች በመነሳት በህገ-መንግስታችንና በተቀመጡ ህጎቻችን መሠረት የሚቋቋሙና የሚፈጠሩ የተቃዋሚ ሀይላት የጀመርናቸውን የልማት የሰላምና ዴሞክራሲአዊ ስረዓት ያፋጥናሉ እንጂ አይጎትቱትም:: ለአገራችን የሚበጁ ሀሳቦች እንዲፈልቁ ምክኒያት ይሆናሉ እነጂ ጅምሮችን አያፈርሱም:: ለዚህ ነው ባንድ ወቅት ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሀቀኛና ትርጉም ያላቸው ተቃዋሚዎች ከተገኙ ግማሽ መንገድ ሄደን እንቀባላቸዋለን ያሉት:: ይህ መተክላዊ አባባል የሚያሳየው ሀቀኛ ተቃዋሚዎች የልማታችን የተረጋጋ ስላምና የደረጀ ዴምክራሲአዊ ስርዓታችን አካል መሆናቸውን ነው::

- የአገራችን ተቃዋሚ ሀይሎች በተለይም በዚህ በውጭ አገር የሚገኘው ከላይ ካነሳናቸው ጭብጦች አንፃር ዕወን የልማታችን ሃይል ናቸው?
- ዕውን የተረጋጋችና አስተማማኝ ሰላም የተፈጠረባት አገር እንድትኖር ይፈልጋሉ?
- ዕውን የዳበረ ዲሞክራሲ እንዲፈጠር አስተማማኝ ደጋፊ ናቸው? ይህን ዘርዘር አድርጎ ማየት ያስፈልጋል

በዚህ በውጭ አገር የተቃውሞ ትግሉን እመራለሁ፣ ብርቱና ጠንካራ ተቃዋሚ ነኝ ብሎ የሚያስበው ሃይል ከመነሻው ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ህጎች ማለትም በህገመንግስት ሆነ በሌሎች ህጎች አያምንም:: የህጎችን መኖር የሚያነሳውም ለእርሱ የሚጠቅሙ መስለው ከታዩት ብቻ ነው:: ለምሳሌ ያህል ፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማሪያም በተለያየ ጊዜ በፃፉትም ሆነ በቃለ መጠይቃቸው ወቅት የታሰሩ የቅንጅት መሪዎችን ሁኔታ ሲጠቅሱ፣ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት መርሆዎች እንደተጣሱ አድርገው ያቀርባሉ:: ፕሮፌሰሩ የቅንጅት ሃይሎች በምርጫ ወቅት ዋነኛ የተባሉ የህገ-መንግስቱ ጭብጦችን (የብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን የመሬት ጥያቄ ወ.ዘ.ተ) እንቀለብሳለን እያሉ ሲደነፉ፣ ለጋውን ዲሞክራሲ ላለማናጠብ የመንግስትንና የኢ.ህ.አ.ዲ.ግን ታጋሽነት ማንሳት የሞት ያህል ይከብዳቸዋል:: ይህን ለአብነት ያህል አነሣን እንጂ የእነዚህ አይነት ምክኒያታዊ ያልሆኑ ክርክሮችን ለቅመን እናቅርብ ቢባል አምድም ጊዜም አይበቃንም::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

በውጭ የሚገኘው የተቃዋሚ ሃይል አገራችን ባለፉት ዓመታት ያስመዘገበችው የኢኮኖሚና የልማት ለውጦች አይኑ እያየ አያስተውላቸውም፣ ጆሮው እየሰማ አያዳምጣቸውም፣ ዕጁ እየዳሰሰ አይጨብጣቸውም፣ አፍንጫው ቢያሸትም መዓዛቸውን አያጣጥመውም:: አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት ...... እንደተባለው ለተገኙ ድሎች ማፍረሻ ምክኒያት ይፈልጋል እንጂ አዎ! ለውጥ አለ! ካለማ የቆመለት ጭፍን ተቃውሞ የማለለት፣ የማጥላላት ፖለቲካ ሊፈርስ ስለሆነ በፍፁም አትታሰብም:: ከዚህ ይልቅ ለውጡ በህንፃ ብቻ የሚታይ ነው፣ የኑሮ ውድነቱ ከፍቶአል፣ እድገቱ የአሀዝ ነው ወ.ዘተ በሚል ለማጥላላት ለማኮላሸት ቀን ከሌት ይሮጣል:: የጀመርናቸው የልማት ተግባራት በውጥን እንዲቀሩ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና መንግስታት ዕርዳታቸውን እዲያቋርጡ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይጥራል:: በአገር ቤት የሚገኙ ወገኖቹ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲቋረጥ፣ የተጀመሩ የመንገድ ስራዎች ባሉበት እንዲቆሙ፣ ውሃ ለማቆር የደረሱ ግድቦች እንዲመክኑ፣ የለጋሽ ወገኖችን ቤት ቀን ከሌት በመቆርቆር የወገኖቹን ኑረሮ ለመዝጋት ይሮጣል:: ይህ ተግባር በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ማንንም ባስደመመ መልክ ሲጧጧፍ የነበረ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የትግል ስልት ነበር:: ታድያ ይህ ኃይል ዕውን የልማታችን ሃይል ነው? የጀመርናቸውን የልማት ጅምሮች እየተከታተለ የሚያጠፋ፣ የሚያጥላላና የፋይናንስ ምንጮቻችን ለማድረቅ ደፋ ቀና የሚል ከሆነ የልማት ሃይል ወይስ ፀረ ልማት?

በሌላ በኩል ይህ በውጭ ራሱን በጭፍን ተቃውሞ ያሰለፈ ሃይል አመጣጡ የራሱ የሆነ ታሪክ ቢኖረውም አገራችን ሰላም ውላ እንዳታድር የማይሸርበው ሴራ የለም:: በፊት በፊት ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሄረሰቦች አገር መሆኗን አለመቀበል ብቻ ሳይሆን ብሄር ብሄረሰቦች የሚለውን ቃል መጥራት ራሱ ከሀዲነትና አገርን መበታተን ነው ብሎ ያስብ ነበር:: አሁን አሁን «ከመወጠር ብዛት በመጣ ልልነት» ምክኒያት ብሄር ብሄረሰቦች እንዳሉ ቢቀበልም የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ከወሰኑ አንድነት የለም በማለት ራሱን የአንድነት ጠበቃ አድርጎ ለማሰለፍ ይጥራል:: በአገር ቤት ህዝቡ በክልል አስተዳደሩ የራሱን እጣ ፈንታ በልማት በማህበራዊ ለውጦች እያረጋገጠ ከሌሎች ህዝቦች ጋር በመፈቃቀድ አንድነቱን እየአጎለበተ ሲመጣ እያአስተዋለ፣ እሱ በዚህ በአሜሪካ ጓዳ ትግሬ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ሱማሊ ወ.ዘ.ተ እየለ የአንዲት አገር ህዝብ መምሰሉ ቀርቶ ለጎን እየተያየ እነዲተላለፍ፣ ሌላው ቀርቶ በዕምነት ቦታዎች እንዳይገናኝ በማድረግ አለያይቶት ይገኛል::



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

ከ80 በላይ ብሄር በሄረሰቦችና ከአንድ መቶ በላይ ቋንቋ በሚነገርባት አገር፣ ለወደ ፊት ዘላቂ የሆነ ሰላም ሊፈጥር የሚያስችል የመፍትሄ ሀሳብ የለውም:: ዛሬ ነፃነታቸውን እያጣጣሙ የሚገኙ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄር ቤሄረሰበቦች እንዳለፉት ዘመናት አድርጎ ለማስተዳደር መሞከር የአገራችንን አንድነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥለው ብቻ ሳይሆን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የሚቻል አይደለም:: ስለዚህም በአንድነት ስም የሚደረግ ፀረ- አንድነት ተግባር ነው:: ለነገሩ በዚህ በውጭ ያለው አክራሪ ተቃዋሚ አይደለም ኢትዮጵያን በዚህ በውጭ ያለውን ህዝብ ከብሄረስብ አልፎ በመደር ከሚከፋፍልበት ደረጃ የደረሰ ነው:: በዚህ በውጭ እንደሚያደርገው ሴራ ሁሉ በአገር ቤት የሚገኙ ወገኖቻችን በሰላም ዕለታዊ ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ በመቀስቀስና ራሱ ባይገባም የትጥቅ ትግሎች እንዲካሄዱ ከመገፋፋት የቦዘነበት ጊዜ የለም:: ባገኘው አጋጣሚ ሆነ በሚያስተላልፋቸው ፕሮፖጋንዳዎች ብሄር በብሄር ብሄረስብ በብሄረሰብ ላይ እንዲነሳና እንደተላለቅ ከመወጠን እስከ መፈፀም ይንቀሳቀሳል:: በመሆኑም ይህ ተቃዋሚ ሃይል ዕውን የአስተማማኝ የሰላም ጠበቃ ነው ወይስ ፀረ ሰላም?

ጤናማ በሆነ ተቃውሞ በግጭትና በፍጭት ውስጥ የሚታዩት በተለያየ መልክ የሚከሰቱ ሀሳቦችና አስተያየቶች ናቸው:: ከዚያ በመለስ በተለያየ ጎራ የሚገኙ ተቃዋሚዎች በማህበራዊና አገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ሰምና ወርቅ ሁነው መታየታቸው የተለመደ ጉዳይ ከመሆኑ አልፎ በምርጫ ተሸናፊው ለአሸናፊው እንኳን ደስ ያለህ በማለት ዴሞክራሲአዊ ተሸናፊነቱን በፀጋ ይቀበላል::

በዚህ በውጭ የሚገኝ ተቃዋሚ ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ማንኛውንም ጉዳይ መቃወም የዲሞክራሲአዊ መብትና የኢትዮጵያ መንግስትን ማዳከሚያ ዘዴ አድርጎ ይወሰደዋል:: በኢትዮጵያ መንግስት ተቀጥሮ የሚሰራ ወይም ላመነበት ዓላማ መንግስትን የደገፈ «ሆዳም፣ ሆድ-አደር፣ ባንዳ» እየተባለ ይብጠለጠላል:: ከዚህ በላይ አልፈው እነሱ ያነሱትን ሀሳብ ያልደገፈ «ወያኔ» ተብሎ ከሌላው አካል እንዲነጠል ይጥራሉ:: ይህም ለእነርሱ የዲሞክራሲአዊ ትግላቸው አካል ነው:: ከዚህም በላይ አልፈው የመንግስትን አላማ ይደግፋል የተባለ ሁሉ የእግዚአብሔር ሰላምታ እንኳ እንዲነፈገው ይሰራሉ:: ይህንም ተግባር ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማየት በቅርብ ጊዜ በሰጡት የፓልቶክ መግለጫ ጉዳዩን አስንተው ከጠላት ጋር ሰላምታ መለዋወጥ እንደማያስፈልግ ለተከታዮቻቸው መክረዋል::

ይህ የተቃውሞ መነሻና መድረሻ የጠፋበት አካል በሰለጠነው አለም በአካል ቢኖርም በተግባር እያሳየ ያለው የተቃውሞ ተግባር ግን ወደ ኋላ የቀረና ከጊዜው ጋር የማይሄድ ነው። ራሱ በሚጠራቸው ስብሰባዎች የማይገኘውን በተለያየ ስድብና ዘለፋ ማሸማቀቁ ሳያንሰው፣ የሱን አስተሳሰብ የማይወክሉ ተቃራኒ አካላት በሚጠሩት ስብሰባ ለመገኘት የሚመጡ ግለሰቦችን መስደብ፣ መዝለፍ፣ ከበር ላይ በመሆን አናስገባም ከማለት አልፎ በአካል እስከ መተናነቅ መድረስ ለእነርሱ የዲሞክራሲው ትግል አካል ነው።

በዚህ በሀይልና በሽብር የተሞላው ተቃውሞ ተግባር በበቂ መጠን ከተጋነነ በኋላ እርስ በእርሱ በፖለቲካ ስም ገቢአቸውን በሚያሳብጡ አከላትና ዌብሳቶች ፍጆታ ይውላል። በዚህ በተለይ በአሜሪካን የሚገኝ ጭፍን ተቃዋሚ በህጋዊ መንገድ ዲፕሎማሲአዊ ግንኙነት ያላቸውን አሜሪካንና ኢትዮጵያን ቢችል ለማቆራረጥ የማያደርገው ሤራ የለም። የኢትዮጵያ ፌደራል ሆነ የክልል ሀላፊዎች ሲመጡ እንዴት በዚህ እኛ ባለንባት አገር ይመጣሉ ከሚለው ጀምሮ በኤምባሲና በቆንስላ ጽ/ቤት ደረጃ የተቋቋሙትን ተቋማትን በማጥላላት ከኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባላት ጋር ለማነጣጠል ከቻሉና ዕድሉን ካገኙም ደግሞ ተቋማቱን ለማዘጋት ወደ ኋላ እንደማይሉ ስራቸው ያረጋግጣል። ከዚህ ተግባራቸው ስንነሳ እነዚህ ሃይሎች የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል ጠበቃ ወይስ የፀረ-ዴሞክራሲ ተግባራት ወኪል?

በአጠቃላይ ከላይ በተለያየ መልክ የተገለፀው በዚህ በውጭ የሚገኝ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የሚገኝበት የሰለጠነ አለም እንዲሁም በተነፃፃሪነት ያለው ትምህርት ብዙ አዳዲስ የልማት፣ የዲሞክራሲና የሰላም አማራጭ ሀሳቦችን በማመንጨት ለአገር ግንባታ ማዋል፣ ለድሃ አገራችን እንደ አንድ ሀብት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። አሁንም የጭፍን ጥላቻ ፖለቲከኞች የሚጋርጡትን ችግር ተቋቁመው አበረታች ስራ እየሰሩ ያሉ ወገኖቻችን ሊበረታቱ ይገባል።

በውጭ የምንገኝ እውነተኛ የዲሞክራሲ ቤተሰቦች ግን፣ ልዩነት በማንኛውም መልክ ሊኖር የሚችልና የሚገባው መሆኑን በመረዳት፣ በሚያስማሙ ጉዳዮች ላይ እየተስማሙ፣ በቀሪዎች ጉዳዮች ደግሞ እተወያዩና እየተቀራረቡ ለአገር መስራት እንደሚቻል በመረዳት የጭፍን ጥላቻ ፖለቲከኞች ሴራ ማክሸፍ ይገባናል። ይህን በማድረግ ብቻ ነው በሀሰት፣ በጥላቻ፣ በስም ማጥፋት፣ በዘለፋ የተመስረተውን የጥላቻ ፖለቲከኞችን ፀረ-ልማት ፀረ-ሰላምና ፀረ-ዴሞክራሲ ዓላማ የምናከሽፈው። ይህን ስናደርግ ብቻ ነው የጀመርነው ፀረ-ድህነት ትግል በአጭር ጊዜ ግቡን የሚመታው። ይህ ከሆነ የለማች፣ የተረጋጋችና የዳበረ ዴሞክራሲን የምትከተል ኢትዮጵያን የምናይበት ጊዜ ቅርብ ይሆናል። ነገም ሌላ ቀን ነውና. . . .



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org